# ያቁሙ

# ከፍተኛ የመተላለፍ ደረጃ ላላቸው በሽታዎች የሚደረጉ ቅድመ ጥንቃቄዎች

(ከመደበኛ ቅድሜ ጥንቃቄዎች በተጨማሪ)

*ጥያቄ ካለዎት፣ እባክዎ የሕክምና ሠራተኞችን ይጠይቁ።*

## ጎብኚዎች አይፈቀዱም

**የግል መከላከያ መሣሪያ በምያደርጉበትና በምያወልቁበት ጊዜ ክትትል የሚያደርግ የሰለጠነ ባለሙያ የግድ መኖር አለበት።**

1) ለንክኪ የተጋለጡትን ለመለየትና ለመከታተል የምረዳ **የክፍል መግቢያ መዝገብ ይፍጠሩ**።
2) **የሰለጠኑ የክክትትል ባለሙያ መጠቀም:** የሕክምና ሠራተኞች (HCW) ታካሚን ስንከባከቡ/ስያክሙ የምከታተል፣ መቆረጥን፣ ማንኛውንም በዓይን የምታዩ ብክለቶችን፣ የግል መከላከያ ስያደርጉና ስያወልቁ የምወጣውን ዕንባና የግል መከላከያ መሣሪያ አደራረግና አወላለቅ ቅደም ተከተል ለሕክምና ሠራተኞች የሚያስረዳ ግለሰብ ነው። የክትትል ባለሙያው፣ የሥራ አጋሩን ስለ ግል መከላከያ መሣሪያ አደራረግና አወላለቅ የሚያስረዳ ከሆነ፣ እንድዝሁ የግል መከላከያ መሣሪያ መጠቀም አለበት።
3) ***ማንኛውም ግለሰብ ከመግባቱ በፊት የግድ:***



**እጅዎን ይታጠቡ።**
**ከታካሚ ወይም ከመሳሪያ ንክኪ በፊት እና በኋላ ኋዋንትዎን ከእጅዎ ሳያወልቁ በአልኮል በመጠቀም (ABHR) እጅዎትን ያሹ።**



**ለሕመምተኛ ብቻ የተፈቀዱ ወይም ሊጣሉ የሚችሉ መገልገያዎችን ይጠቀሙ። መገልገያ መሣሪያውችን የተረጋገጡ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን በመርጨት ያጽዱ።**



**ከክፍል ውጪም ሆነ ከክፍል ውስጥ ስትሆኑ ተገቢውን የአደራረግና አወላለቅ መመሪያን በመከተል ፈሳሽ ተከላካይና ውኃ የማስተላልፍ ሙሉ ጋዎን ይልበሱ። ምንም ዓይነት ቆዳ መታየት የለበትም።**



**ፈሳሽን የሚቋቋምና ውኃን የማያስተላልፍ ቢያንስ እስከ ግማሽ ባት መሸፈን የሚችል ቡት ያድርጉ።**



**የዓይን መጠበቂያ፣ የፊት መሸፈኛና መነጽር ይጠቀሙ**



**የሚለጠጥ ማሰሪያ ያለውን ጓንት ያድርጉ። ሁለት ጥንድ ጓንቶች መልበስ አለባቸው። ውጨኛው የጓንት ክፍል የሚለጠጥ ማሰሪያ ሊኖረው ይገባል።**



**National Institute for Occupational Safety and Health(NIOSH, ብሔራዊ የሙያ ደህንነት እና ጤና ተቋም)-ደኅንነቱ የተረጋገጠ መተንፈሻ ይጠቀሙ። (N95/PAPR/CAPR)**

***የግል መከላከያ መሣሪያዎች (PPE)***
***የግል መከላከያ ስያደርጉና ስያወልቁ Centers for Disease Control and Prevention (CDC, የበሽታ መቆጣጠሪያ እና መከላከያ ማእከል)ን መመሪያ ይከተሉ።***

**ከበር ውጪ ያሳዩ። ታካሚው ከወጣ፣ ክፍሉ ሙሉ በሙሉ ከጸዳ በኋላ ምልክቱን ያንሱ።**

# ከፍተኛ የመተላለፍ ደረጃ ላላቸው በሽታዎች የሚደረጉ ቅድመ ጥንቃቄዎች

## የግል መከላከያ መሣሪያዎች (PPE)

*በ ኤች.ኤል.ሲ. የታካሚ እንክብካቤ ወቅት* የግል መከላከያ ስያደርጉና ስያወልቁ Centers for Disease Control and Prevention (CDC, የበሽታ መቆጣጠሪያ እና መከላከያ ማእከል)ን ዝርዝር መመሪያ ይከተሉ።

## የCDC የድርጊት ዘመን:

*"የግል መከላከያ መሣሪያ በምጣልበት አከባቢ፣ ለግል መከላከያ መሣሪያ መጣያ፣ እጅ መታጠቢያ እና ግል መከላከያ መሣሪያ የሚጣልበት ቦታ እንደዚሁም በቀላሉ በፀረ-ተባይ ማጽጃ መጽዳት የሚችል መቀመጫ ቦታ ማለትም ሠራተኞች ተቀምጠው የቡት መሸፈኛ የምያወጡበት ሊዘጋጅ ይገባል። የተጠቀሙበትን ግል መከላከያ መሣሪያ መጣያነት የሚያገለግሉ የተበከሉ ቆሻሻዎችን የማያፈስ ማጠራቀሚያ ያዘጋጁ።* በሕክምና ሰራተኞች የግል መከላከያ መሣሪያ የማውለቅ ተግባርን ጨምሮ፣ የግል መከላከያ መሣሪያ ማስወገጃ ቦታን ፀረ-ተባይ መርጨትና የማጽዳትን ያከናውኑ።

**ተቋሙ ከታካሚው ክፍል ውጭ ያለውን ኮሪደር እንደ የግል መከላከያ መሣሪያ ማስወገጃ ቦታ የግድ መጠቀም ካለበት፣ ኮሪደሩን በትራፊክ እንዳይጨናነቅ አካላዊ መሰናክሎችን በመገንባት ክፍሉ በረንዳ እንድኖረው (ቦታ ከእሳት-ኮዶች ጋር የተጣጣመ መሆኑን ያረጋግጡ) ያድርጉ። የኤች.ኤል.ሲ. ጥንቃቄ ለሚሹ ታካሚዎች የሚመከሩ የኢንፌክሽን መከላከል ልምዶችን በአግባቡ የሰለጠኑ አስፈላጊ ባለሙያዎች ካልሆነ በስተቀር ወደዚህ አዳራሽ መግባትን ይከለክላሉ።**

### ለሞት ሊዳርጉ የሚችሉ ከፍተኛ በሽታ አምጪ/አስተላላፊ ተዋህሲያን እንደ:-

- እንደ ኢቦላ ቫይረስ ያሉ የቫይራል ሄሞሬጂክ ትኩሳት
- በመከሰት ላይ ያሉ ሽታ አምጪ/አስተላላፊ ተዋህሲያንና ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርሱ ተላላፊ በሽታዎች

### ምግቦችና ዕቃዎች

- **ሊጣሉ የሚችሉ** የምግብ ትሪዎችና ሳህኖችን ይጠቀሙ።

### የቆሻሻ እና የአልጋ ልብስ ንጽሕና አጠባበቅ

- የታካሚ ክፍል ውስጥ ያለውን በባዮአዛርድ ውስጥ፣ ሊያፈስ በማይችል ከረጢት ውስጥ ያስቀምጡ እና በሽታ አምጪ ለሆኑ ህዋሳት ***ምድብ A*** ወይም ምድብ B የህክምና ቆሻሻ ማስወገጃን የተቋሙን መመሪያዎችን በመከተል ያስወዱ።

### ክፍልን ማጽዳት

- የU.S. Environmental Protection Agency(የዩኤስ የአካባቢ ጥበቃ ኤጀንሲ) ፀረ-ተባይ ኬሚካል በመጠቀም የአሳሳቢ የሆኑ በሽታ አምጪ ተህዋስያንን ከአከባቢው እንድጠፉ መደረግ አለበት። የታካሚ እንክብካቤ ቦታን እና ሁሉንም በተደጋጋሚ የተነካኩ እቃዎችን በየቀኑ ያጽዱ። ይህ እንደ የታካሚ እንክብካቤ ተግባር ወደ ክፍል የሚገቡትን ተጨማሪ የጤና አጠባበቅ ሰራተኞችን ቁጥር ለመገደብ በእንክብካቤ ቡድን ብቻ መከናወን አለበት።

### የታካሚ ምደባ

- ***የግል ክፍል አስፈላጊ ሁኖ***, በተለይ የራሱን የገላ መታጠቢያ ያለው ቢሆን ይመረጣል። ለበሽታ አምጭ ተዋስያን ጉዳይ በይበልጥ የአየር ወለድ በሽታ መከላከያ ክፍል (AIIR) ቅድሚያ መስጠት።

### መሣሪያና አቅርቦቶች

- ክፍል ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ መሣሪያና አቅርቦቶችን ብቻ ይቀመጡ።
- ለታካሚ ብቻ የተፈቀዱ ወይም ልጣሉ የሚችሉ መገልገያዎችን ይጠቀሙ።
- በተቋሙ ፖሊሲ መሠረት ድጋሚ የሚያገለግሉ መሣሪያ/የታካሚ ክፍል በተረጋገጠ EPA ፀር-ተባይ መርጨትና ማጽዳት::

### ትራንስፖርት

- ከማጓጓዝዎ በፊት የኢንፌክሽን መከላከልን ወይም የህዝብ ጤናን ያማክሩ።

***<u>የሂንፌክሽን መከላከል ምክሬ ሀሳብ ካገኙ ብቻ ቅድሜ ጥንቃቄን ያቋርጡ።</u> ቅድሙ ጥንቃቄ ከተቋረጠና ክፍሉ ከጸዳ በኋላ ምልክቱ Environmental Services (በአከባቢ አገልግሎት) ሠራተኞች እንድነሳ ይደርጋል።***

**420-591 April 2024 Amharic**

ይህን ሰነድ በሌላ ቅርጸት ለማግኘት፣ ወደ 1-800-525-0127 ይደውሉ። መስማት የተሳናቸው ወይም መስማት የሚቸግራቸው ደንበኞች ወደ 711 (Washington Relay) መደወል ወይም ወደ doh.information@doh.wa.gov ኢሜይል ማድረግ ይችላሉ።

Washington State Hospital Association

Washington State Department of HEALTH